# <u>የአፍሪካ ቀንድ በፕሮፌሰር መስፍን እይታ</u>

መለስ ዓ.

አንጋፋው ተመራማሪና ፖለቲከኛ ፕሮፌሰር መስፍን ወልደማርያም "አደጋ ያንዣበበት የአፍሪካ ቀንድ" በሚል ርዕስ ያዘጋጁትን መጽሐፍ ሰሞኑን ለንባብ በቅቷል፡፡ ይህ ፀሐፊም ቀደም ሲል የፕሮፌሰሩን ሥራዎች የማየት ዕድል ስለነበረው መጽሐፉን በጉጉት አንብቦታል፡፡ ስለ ፕሮፌሰር መስፍን ሥራዎችና የፖለቲካ ሕይወት መዘርዘር የዚህ ጽሁፍ ፍላጐት አይደለም፡፡ ስለምን ፕሮፌሰሩ ለብዙ አስርት ዓመታት በሀገራቸው የፖለቲካ፣ ኢኮኖሚ እና ማኅበራዊ መስተጋብር ንቁ ተሳታፊ በመሆናቸው ለብዙ ወገን እንግዳ አይደሉም፡፡

በሀገራችን የመጻፍ ባህል አልዳበረም፡፡ ይህ ግን ፕሮፌሰር መስፍንን አይመለከትም፡፡ ፕሮፌሰር መስፍን የአሁኑን ጨምሮ ከደርዘን በላይ መጽሐፍትን በአማርኛ እና በእንግሊዝኛ ቋንቋዎች ለንባብ አብቅተዋል፡፡ ፕሮፌሰር መስፍን አሁን ያሳተሙት መጽሐፍ 237 ገጾች አሉት፡፡ በአፍሪካ ቀንድ ግጭትና ጦርነት፣ ሽብርና ሽብርተኝነት፣ የአረቦች ሕዝባዊ አብዮት፣ ወዘተ ላይ ከሚያተኩሩት አስር ርዕሶች በተጨማሪ

በ1951 ዓ.ም. ገና በ29 ዓመታቸው ያዘጋጁትን "የአጋዴን የፖለቲካ ጆኦግራፊ" እንዲሁም እ.ኤ.አ. 1971 በአሜሪካ በጆርጅታውን ዩኒቨርስቲ "Ethiopia and the Indian Ocean" በሚል ያቀረቡትን ጽሑፍ በተጨማሪ አክለዋል፡፡ በሁለቱም ጽሁፎች ከኢትዮጵያ የፖለቲካ፣ የፀጥታ እና ኢኮኖሚ ጥቅም አንጻር ያቀረቧቸው ትንተናዎች ከጊዜያቸው የቀደሙ ናቸው፡፡ በሳል ሆነው አግኝቻቸዋለሁ፡፡ ፕሮፌሰር መስፍን ጽሑፎቻቸውን ከራሳቸው ሕይወት ጋር በማስተሳሰር ስለሚያቀርቡ ልጅነታቸውን በዓይነ ህሊናህ ለመሳል ያስችላል፡፡ አገቱኒ በሚለው መጽሐፋቸው ላይ የወጣቱን መስፍን ወ/ማርያም ቦክስ ወዳድነት ያስባል፡፡ በአሁኑ መጽሐፉ ደግሞ ፕሮፌሰሩ ከችጋር ጋር መጀመሪያ የተዋወቅሁት ልጅ ሆኜ የኢጣልያ ወረራ ካበቃ በኋላ ነው ይላሉ፡፡ "ክፉ ረሃብ አዲስ አበባ ገብቶ እኔም ለመፍትሔ የድርሻዬን ለማበርከት ከእንጦጦ እንጨት ለቅሜ ተሸክሜ ጊዮርጊስ ገበያ ድረስ ወስጄ ሸጫለሁ" ይላሉ ፕሮፌሰሩ፡፡

ብዙ ፀሐፊዎች የአፍሪካ ቀንድ ትርምስና ረሃብ የማያጣው ክልል ነው በሚለው አገላለጽ ይስማማሉ፡፡ ፕሮፌሰሩም የአካባቢው ሁለት መገለጫ ችግሮች ግጭትና ችጋር እንደሆኑ ያቀርባሉ፡፡ ይህ ፀሐፊም በዚህ መደምደምያ ይስማማል፡፡

አካባቢው በጦርነት ተወልደህ በጦርነት የምታረጅበት ክልል ነው፡፡ ከየትኛውም የአፍሪካ ክፍለ አህጉር በላይ ከፍተኛ ቁጥር ያለው ግጭት በዚህ አካባቢ ይገኛል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ አፍሪካ የመከራና የስቃይ አህጉር፤ የአፍሪካ ቀንድም ግርግር የማያጣው መሆኑን ፀሐፊው በተለያዩ አስረጅ አቅርበዋል፡፡ ይህ ፀሐፊ ከፕሮፌሰር መስፍን ጋር በመፅሐፉ ላይ ከተጠቀሱት ውስጥ ከእነዚህ በተጨማሪ በበርካታ ነጥቦች የሚስማማ ቢሆንም ሰፊ አስተያየት ለማቅረብ በጊዜና በቦታ ለመወሰን ይገደዳል፡፡

የአፍሪካ ቀንድ ሀገሮች በፉክክርና በመጠላለፍ ሀብታቸውንና የዜጐቻቸውን ሕይወት በከንቱ ከሚያጠፉ በትብብር ወደ እድገትና ብልጽግና መሸጋገር ይገባቸዋል፤ በጦርነት የሚገኘው ኪሳራ ነው በሚለው በፕሮፌሰር መስፍን መደምደምያ ተገቢ ነው ብሎ ያምናል፡፡ ሁለተኛ በኢትዮጵያና ኤርትራ መሀከል የሚካሄድ ግጭት ከሀገሮቹ አልፎ በሌሎች አጐራባቾች ላይ የበለጠና የከፋ ችግር ሊያስከትል ይችላል የሚለውም እንደዛው፡፡ በሶስተኛ ደረጃ የሶማሊያ መንግሥት አልባ መሆን ኢትዮጵያን ጨምሮ ለማንም እንደማይጠቅም ፕሮፌሰር በሚገባ አስቀምጠዋል፡፡ "ዛሬ የሶማሊያ መፈረካከስ ጥሩ መስሎ የሚታያቸው ሰዎች አሉ፤ ይህ የተሳሳተና ከስሜት የመነጨ ዕይታ ነው" ሲሉ ይገልጹታል፡፡ ትክክል ነው፡፡

ከፀሐፊው ጋር ከምስማማባቸው ውስጥ ይህን ያህል ካልኩ ለዚህ መጣጥፍ መነሻ ወደ ሆነኝ ሃሳብ በአክብሮት ልቀጥል፡፡ በፀሐፊው ዕይታ የመጽሐፉ ዋና ዋና እንከኖች በሶስት ከፍሎ ማስቀመጥ ይቻላል፡፡ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የጭብጥ መዛነፎች፣ በጭፍን ጥላቻ ላይ የተመሰረቱ አስተያየቶች፣ የተምታቱ መደምደሚያዎች እና ለቀጣዩ የወጣት ትውልድ ተጻፈ ከሚባል የማይጠበቁ ዘለፋዎች ይስተዋላል፡፡ ይህ የፌደል ለቀማ ያለማድረጉን እና የሃሳብ ግልጽነት ችግርን እንዳለ በመተው ነው፡፡ ይህ ፀሐፊ አደጋ ያንዣበበት የአፍሪካ ቀንድ በሚል ርዕስ በቀረበው መጽሐፍ ላይ አሉ ከሚላቸው የፕሮፌሰር መስፍን ወ/ማርያም ግድፈቶች ውስጥ ዋነኞቹ የሚከተሉት ናቸው፡፡

<u>አንደኛ</u>

ቀደም ሲል ለመግለጽ እንደተሞከረው መጽሐፉ ዓለምዓቀፍ፣ ክፍለ አህጉራዊና ሀገራዊ ጉዳዮች ላይ ትኩረት አድርጓል፡፡ ከመግቢያው (ገጽ-7) አሜሪካኖች ቢንላዲንን እንዴት እንደገደሉት ሲገልጹ "... የጠኪስታንን መንግሥት ማስፈቀዱ ቀርቶ ሳያሳውቁ ገድለው ሬሳውን ወሰዱት ይላሉ" ከሁለት ቅጠሎች በኋላ ደግሞ ቢንላዲን በጠኪስታን የሚኖርበትን ቤት ካገኙ በኋላ ሄደው ከመግደላቸው በፊት

ለጠኪስታን ባለሥልጣኖች አለመንገራቸው በእነሱ እምነት እንደሌላቸው የሚያመለክት ነው በማለት ሃሳባቸውን ያብራሩታል፡፡ በመጀመሪያ በጠኪስታን የሲቪል መንግሥት ይኑር እንጂ ፈላጭ ቆራጩ ወታደሩ በሆነበት መንግሥትን ምን ያማክሩታል? ከቢን ላዲን የመጨረሻ ሰዓት ጋር ያለውን ሁነት የተከታተለ ሰው እንደሚያውቀው አገዳዳሉን በተመለከተ ያለው ሁለት ትንተና ነው፡፡ አንደኛው የፕሮፌሰር መስፍን ነው፡፡ ይሁን እንጂ አሜሪካኖቹ ቢን ላዲንን ለመግደል ፓኪስታኖችን ጨምሮ የማንንም ፍቃድ ይጠይቃሉ ተብሎ እንዴት ይጠበቃል? ብዙ ተንታኞች እንደሚስማሙት ቢን ላዲን ከጠኪስታን የስላላ ድርጅት አይ.ኤስ.አይ (Interservices Intelligence) እውቅና ውጭ አልነበረም፡፡ በአሜሪካ የብሪታንያ አምባሳደር ሰር ክርስቶፎር ሜየር በአንድ ወቅት እንዳሉት የጠኪስታን የስለላ ድርጅት ለቢን ላዲን ክለላ ሰጥቶታል፡፡ ስለሆነም የአልቃይዳውን መሪ ለመግደል ጠባቂዎቹን ማስፈቀድ አይገባም፡፡

የስለላ መዋቅሩ እና የጦር ኃይሉ ቢን ላዲንን በተለይ በአፍጋኒስታን የሚካሄደውን ዘመቻ በአጠቃላይ በተመለከተ ከመንግሥት የተለየ አቋም አላቸው፡፡ መንግሥት የአሜሪካንን ዛቻ በመፍራትና የኢኮኖሚ ድጋፍ በመፈለግ ፀረ አልቃይዳ

ዘመቻውን ይደግፍ እንጅ የፀጥታ አካላት ግን ከፕሬዚደንት ሃሚድ ካርዛይ መንግሥት ይልቅ ታሊባኖች ካቡል ውስጥ መንግሥት ቢሆኑ አይጠሉም:: የጠኪስታን መንግሥት ቢን ላዲን አቦታባድ ውስጥ ሲገደል አይኔን ግንባር እንዲል ያደረገው በሀገር ውስጥ የሚነሳበትን ተቃውሞ በመስጋት እንደሆነ ይነገራል:: የአሜሪካና የጠኪስታን ውዝግብም ቢሆን ከቢን ላዲን መገደል በፊት የነበረ ነው:: ልዩነቱ የስትራቴጂ ነው:: አሜሪካ በወታደራዊ ስትራቴጂ ስታተኩር የጠኪስታን መንግሥት በሀገሪቱ የጦር ኃይል እጁ ተጠምዝዞ ለክብ ጠረጴዛ ውይይትና ከታሊባን ጋር ለሚደረግ እርቅ ቅድምያ እንዲሰጥ ጠንካራ አቋም አለው:: ፕሮፌሰር መስፍን የሳቱት የመጀመሪያው ነገር ይህ ነው::

<u>ሁለተኛ</u>

አፍሪካ ቀንድ በሀብት በኩል ስናይ ምንም ያህል የለውም (ገጽ 147) ካሉ በኋላ "አሁን ደቡብ ሱዳን ትንሽ ነዳጅ ተገኝቷል:: ከዚህ በተረፈ አፍሪካ ቀንድ ሙልጭ ያለ ድህነት ነው ያለው፣ ያለው ችግር ነው ሲሉ ይደመድማሉ::" ከሶስት ገጽ በኋላ ደግሞ የድህነታቸው ምክንያት የተፈጥሮ ሀብት ማጣት ወይም የሕዝቡ ስንፍና አይደለም ሲሉ ይሞግታሉ:: ይህ እዚህ እና እዚያ የሚረግጥ ሃሳብ ነው:: እርግጥ የአካባቢው

ሀገሮች በችግር ተቀስፈው መያዛቸው ትክክል ነው:: ይሁን እንጂ ሀገሮቹ በጦርነትና በረሃብ ለዘመናት ሲታመሱ ሀብታቸውን (ልዕለ ምድርም ይሁን ትህተ ምድር) መጠቀም አልቻሉም እንጂ ምንም ስለሌላቸው አይደለም የሚለው በምንም ማጣቀሻ የተደገፈ አይደለም:: አለም የለምም ለማለት ሀገሮቹ ሰላም ውለው መቼ ሰላም አደሩ::

<u>ሶስተኛ</u>

ወደ አካባቢው ሀገሮቹ ሲመጡ አንጻራዊ ሰላም ያላት ሀገር ተደርጋ የቀረበችው ኬንያ ናት:: ኬንያ በታሪኳ ወራም ተወራም እንደማታውቅ ይነገራል:: ይሁን እንጂ በዓመቱ መጀመሪያ የኬንያ ወታደሮች አልሸባብን እያሳደዱ ደቡባዊ ሶማሊያ ከገቡ ሰነባብተዋል:: የፕሬዝዳንት ሙዋይ ኪባኪ አስተዳድር ወታደሮቹን ወደ ሶማሊያ ያስማራው ሁለት የውጭ ሀገር ቱሪስቶችን በመጥለፋቸው የኬንያ የዳበረ የውጭ ሀገር ጐብኚዎች ንግድ እንዳያበላሸባቸው እንደሆነ በመጽሐፉ ላይ ተገልጿል:: ይሁን እንጂ ኬንያ ለሁለት ቱሪስቶች ስትል አልያም የጭስ አልባው ኢንዱስትሪዋ እንዳይጐዳባት ብላ አይደለም ወደ ጦርነት የገባችው:: ይህ እንደ አንድ ሰበዝ ሊቀመጥ ይችላል:: በእኔ አስተያየት ይህ የቱሪስቶች ጥቃት ጦርነቱ የተጫረበት (immediate cause) ምክንያት እንጂ

መነሻው አይደለም፡፡ "ዘመቻ ሀገር ነጻ ማውጣት" – ይሉታል ኬንያውያን – መንግሥት ለረዥም ጊዜ በሚስጥር ሲዘጋጁበት እንደነበር ይታወቃል፡፡ የኬንያ መንግሥት ለዚህ ዘመቻ ስኬታማነት ሲል ሼክ መዶቤ እና ፕሮፌሰር ጋንዲ በሚባሉ የሶማሊያ ፖለቲከኞች የሚታዘዝ ሶስት ሺህ ያህል ታጣቂ ኃይል ለረዥም ጊዜ ሲያሰለጥን ቆይቷል፡፡ በዕቅዱ መሠረት በአሁኑ ወቅት ኬንያ ደቡባዊ ሶማሊያ ውስጥ ጁባ የሚባል አስተዳደር በማቋቋም የመከላከያ ቀጣና (Buffer Zone) በመፍጠር ፀጥታዋን የመጠበቅ ፍላጐት አላት፡፡ እውነታው ይህ ነው፡፡ የኬንያ መንግሥት መወቀስ ካለበት አልሸባብ ናይሮቢና ሞምባሳን መናኸሪያው ሲያደርግ ዝም ማለቱ ነው፡፡ ከባህር ላይ ዘረፋ ባገኘው ገንዘብ ኢኮኖሚውን ተቆጣጥሮታል፡፡ የኬንያ መንግሥት አሁን እያወራረደ ያለው እ.ኤ.አ. 2006 የኢትዮጵያ ጦር ወደ ሶማሊያ ሲገባ ዳር ቆሞ ተመልካች የሆነበትን ሂሳብ ነው፡፡

<u>አራተኛ</u>

በዚህ የፕሮፌሰር መጽሐፍ ውስጥ ሰፊ ሽፋን ካገኙ ሀገሮች ውስጥ ሶማሊያ ትጠቀሳለች፡፡ ተመራማሪው በሶማሊያ ጉዳይ ብዙ ብለዋል፡፡ ቀደም ሲልም ሶማሊያ አስቸጋሪ ሀገር (the

problem child) ናት ሲሉ ሰይመዋታል፡፡ ሶማሊያ አሁን ያለችበትን ሁኔታ ሲዳስሱ "የጐሰኛነት፣ የጥፋት ጉዞ፣ የማይበርድና የማይታገድ መሆኑን ከተረዱ በኋላ ሶማሊያን ከባሰ የጥፋት ጉዞ ለማዳን ከጐሰኛነት ወደ ኃይማኖት የተሸጋገር ዘዴ የተሻለ ውጤት የሚያሰገኝ መስሏቸው የእስልምና ንቅናቄ ተጀመረ" ብለው ጽፈዋል (ገጽ 128)፡፡ ይህ አስተያየት በሶማሊያ የተፈጠረውን የእስልምና ንቅናቄ የትላንት የሚያስመስል በመሆኑ ስህተት ነው፡፡ በሶማሊያ የእስልምና እንቅስቃሴ እ.ኤ.አ. 1960ዎቹ የተጀመረ እንደሆነ ድርሳናት ያሳያሉ፡፡ ሌሎች ተመራማሪዎች ደግሞ ጊዜውን ወደ 1950ዎቹ ይወስዱታል፡፡ አንዳንድ ፀሐፊዎች በግብጽ ከተቀጣጠለው የሙስሊም ወንድማማቾች ንቅናቄ መስፋፋት ጋር ያያይዙታል፡፡ በሶማሊያ እስላማዊ አመለካከት እንዲነግስ በግብጽ የአልአዛር ዩኒቨርስቲ እና የሀገሪቱ ሬዲዩ ጣቢያዎች ሌት ተቀን ሰርተዋል በሚለው ስምምነት አለ፡፡ በተወሰነ ደረጃም ተሳክቶላቸዋል፡፡ እስላማዊው እንቅስቃሴ በዚህ መልኩ ቢስፋፋም በፕሬዝዳንት ሲያድ ባሬ ዘመን በታወጀው የሶሻሊዝም ርዕዮት ተጽዕኖ ሳቢያ ህቡዕ ለመግባት ተገዶ ነበር፡፡ ፕሮፌሰር እንደሚያውቁት የኮሌኔል ጣሂር አዌስ (ከአልሸባብ መሪዎች አንዱ) ከጦር ኃይል የተባረሩትና ሲያድ ባሬ አስር

ሼኮች ላይ እርምጃ ወሰደው የገደሏቸው ከዚሁ የኃይማኖት አክራሪነት ጋር የተያያዘ ነበር፡፡

ከዚህም በተጨማሪ ሶማሊያውያን የጦር አበጋዞች መፍትሔ ሊያመጡ ባለመቻላቸው ሕዝቡ ተስፋ በመቁረጥ ለእስላማዊ ኅብረት (አይ.ሲ.ዩ) እድል ለመስጠት ቢወስንም ሶማሊያውያን መጀመሪያ ጐሳቸውን ከዚያ ደግሞ ኀይማኖታቸውን እንደሚያስቡ የታወቀ ነው፡፡ የኀይማኖት አክራሪት ሶማሊያውያንን አይገልጹም፡፡ በተለይም አሁን አልሸባብ ከተለያዩ የዓለም ሀገሮች በመጡ አሸባሪዎች በመያዙ ሶማሊያውያንን ይወክላል ማለት አይቻልም፡፡ ከዚሁ የሶማሊያ ጉዳይ ሳንወጣ ስለ አልሸባብ መዳከም ሲገልፁ "በ2003 ዓ.ም. መጨረሻ ላይ አልሸባብ የተዳከመው የሽግግር መንግሥቱን መቋቋም ተስኖት ይሁን ወይም ችጋር (በሀገሪቱ የተከሰተውን) በውል ባይታወቅም አፈግፍጐ ከሞቃዲሾ ወጣ" ብለዋል (ገጽ 129)፡፡ በ29ኝ ዓመታቸው በጻፉት ጽሁፍ ጠንከር ያሉ አስተያየቶችንና ትንተናዎችን ያስነበቡን ፕሮፌሰር መስፍን ምክንያቱ ጠፍቶባቸው ከሆነ ሌላ ሰው ቢጠይቁ አልያም የራሳቸውን ትንሽ የቤት ሥራ ቢሰሩ መልሱ ሩቅ አይሆንባቸውም ነበር፡፡ ምክንያቱ በጣም ግልጽ ነው፡፡ አልሸባብ ከደቡብ እና ማዕከላዊ ሶማሊያ እንዲሁም ሞቃዲሾ ተመቶና

ተገፍቶ የወጣው በአሚሶም እና በሽግግሩ መንግሥት ነው፡፡ እርግጥ ነው ችጋሩ እና በመሪዎቹ መሐከል የተፈጠረው የታክቲክ ልዩነትና ሽኩቻ ለሽንፈቱና መዳከሙ አስተዋጽኦ አድርገዋል፡፡ አልሸባብ በከተማ የሽምቅ ውግያ ጠንካራ ነው፡፡ ሞቃዲሾ ባካራ ገበያ ውስጥ ሃምሳ ሜትር የሚሆን ይዞታውን ለመያዝ እስከ ሶስት ቀን የሚፈጅ ውግያ መካሄዱ ይታወቃል፡፡ ይሁን እንጂ አልሸባብ በሁለት እና ሶስት አሸባሪዎች እንጂ በትልቅ ኃይል ተደራጅቶ የሚያጠቃ፣ የሚከላከልና ስልታዊ ማፈግፈግ የሚያደርግ ቡድን እንዳልሆነ በተግባር ተረጋግጧል፡፡ ሌላው ፑንትላንድ እንደ ሶማሌላንድ ሁሉ ተነጥሎ የራሱን መንግሥት አቋቁሟል ሲሉ በተደጋጋሚ ገልፀዋል፡፡ ሌላ ስህተት፡፡ እስከሚታቀው ድረስ ፑንትላንድ በሶማሊያ ስር ያለች ራሷን የቻለች (Semi autonomous) አስተዳደር እንጂ እንደ ሶማሌላንድ አንድም የመገንጠል ጥያቄ የላትም፡፡ አብዛኛው የዳሮድ ጐሳ ከሚኖርባት ፑንትላንድ የሚወለዱት ሟቹ አብዱላሂ ዩሱፍ የሶማሊያ የሽግግር መንግሥትን የመሩት ለዚሁ ነው፡፡ ፕሮፌሰር ሶማሊያን በአራት ይከፍላሉ፡፡ ሞቃዲሾ፣ ፑንትላንድ፣ ሶማሌላንድ እና ኪስማዩ በሚል፡፡ ጋልሙዱግን የመሰሉ ክልሎች የት ይወድቃሉ? በሕዝብም ሆነ በክልል (ጆኦግራፊ) ሶማሊያ እንዲህ የተከፋፈለች አይደለችም፡፡

ሞቃዲሾና ኪስማዮ ከተሞች፣ ፑንትላንድና ሶማሌላንድ ግን ክልሎች ናቸውና በምን መስፈርት ሶማሊያን ከፋፍሎ የሚታዩበት መነጽር እንደሆኑ አይታወቅም:: ሞቃዲሾና ኪስማዮ የብዙ ጐሳ መኖሪያዎች (Multi-ethnic) ናቸው:: ሶማሌላንድ የሶስት የዲር ንዑስ ጐሳዎች፣ ፑንትላንድ ደግሞ የስድስት ንዑስ የዳሮድ ጐሳዎች መኖሪያ ክልል ነው:: ስለዚህ መስፈርቱ ለአንባቢም ለባለሙያም ግልጽ አይደለም::

## አምስተኛ

መጽሐፉ የገለልተኛነት (Objectivity) ችግር አለበት:: ፕሮፌሰሩ ሚዛናዊነት ይጐድላቸዋል:: ፕሮፌሰር መስፍን በአፄ ኃ/ስላሴ ዘመን ኢትዮጵያ በአፍሪካ አንድነት ድርጅት ጉልህ ስፍራ እንደነበራት፣ የአፍሪካ ማዕከል ለመሆን መብቃቷን፣ በሀገሮች መሀከል የማግባባት ሥራ በማከናወን የሚያኮራ ውጤት ማስመዝገቧን፣ እሳቸው በስም ባይጠቅሷቸውም በእድሜም ይሁን በአስተዳደግ ያልተገሩ ያሏቸው ጐረምሶች ግን ወንበር እየያዙ ሀገሪቱን ለውርደት እንዳደረጉ የአይን ምስክር መሆናቸውንም ገጽ 56 ላይ ጽፈዋል:: ይህ ፀሐፊ ስለአፄ ኃ/ስላሴ በሰጡት አስተያየቶች ይስማማል:: ፕሮፌሰሩ ዘለፋቸውን ትተው በጀመሩት መንገድ ቀጣዮቹን መንግሥታት ይህን ሰርተዋል ያንን አልሰሩም ብለው ቢቀጥሉ

ተዓማኒነታቸውን ያጐላው፤ የሞራል ልዕልናቸውን ያገዘፈው ነበር፡፡ ይህን ለማድረግ ድፍረቱን አጥተዋል፡፡ መንግሥታቱ ፍፁም አልያም ሰማያዊ አይደሉም፡፡ እንኳን ሀገር ጠርቶ መምራት ያሉትን ፈተናዎች ከፕሮፌሰር በላይ ምስክር የለም፡፡ ደርግን ለዓመታት የወጉት ጠ/ሚኒስትር መለስ ጁንታው ለአፍሪካ ሀገሮች ነጻነት ያደረገውን አዎንታዊ አስተዋጽኦ አይክዱትም፡፡ ለነገሩ አውቆ የተኛን ቢቀሰቅሱት አይሰማም ነው፡፡ ፕሮፌሰር መስፍን ከመንግሥት ጋር አይንና ናጫ ናቸው፡፡ ሀገሪቱን እየመራ ያለው መንግሥትና ፓርቲ ቢያንስ ቢያንስ አፄ ኃ/ስላሴ ያቆሙትን የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ጽ/ቤት ከአዲስ አበባ እንዳይነሳ ማድረጉን እውቅና አለመስጠት ንፉግነት ነው፡፡ የሊብያው ጋዳፊ እና የሴኔጋሉ አብዱላይ ዋድ የአፍሪካ ኅብረት መቀመጫን ከአዲስ አበባ ለማንሳት ያደረጉትን ጥረት በማክሸፍ የአፍሪካ ዋና ከተማነቷን ማስጠበቅ ተችሏል፡፡ በአፍሪካ ኅብረት ምስረታ ኢትዮጵያ ያላት ሚና፣ በቡድን 8፣ በቡድን 20፣ ወዘተ ያላትን ንቁ ተሳትፎ እንዴት መካድ ይቻላል? ፕሮፌሰሩ አቶ መለስና ኢ.ህ.አ.ዴ.ግን መጥላት መብታቸው ነው፡፡ ሀቅን መሸፈጥ ግን ነውር ብቻ ሳይሆን ተደራሲያንን መናቅ ይመስለኛል፡፡ ቦረናዎች ለጥላቻ መድሐኒት የለውም የሚል አባባል አላቸው፡፡ ፕሮፌሰር መስፍን መጽሐፉ ውስጥ እልህ የአእምሮ ዳፍንትን ያስከትላል

ይላሉ። ተመሳሳይ እልህ ግን በርካታ ቦታ ይንፀባረቃል። ፕሮፌሰርን ጨምሮ ፀሐፊዎቻችን ከራሳቸው ስሜት፣ መውደድ እና ጥላቻ ነጻ ሆነው ሥራዎቻቸውን እንዲያስነብቡን እንፈልጋለን። ፕሮፌሰር የኢትዮጵያ ሠራዊትን የሰላም ማስከበር አስተዋጽኦ በአንድ መስመር እንኳ መግለጽ አልቻሉም። የኢትዮጵያ የመከላከያ ኃይል በቡሩንዲ፣ ሩዋንዳ፣ ላይቤሪያ የንፁሐንን እንባ አብሷል። ፕሮፌሰር ኢትዮጵያ ወደ ዳርፉር ለሰላም ጦሯን ልካለች ይባላል ሲሉ ጽፈዋል። ሽሙጥ ይሆን? ይልቁንም የኢትዮጵያን የዲፕሎማሲ ጥበብ በጨረፍታ ማየትም ተስኗቸው እንጂ በሰሜንና ደቡብ ሱዳን መካከል በሰሞኑ ግጭት አቢዬ ላይ እንዲዘመት ሁለቱም ባላንጣዎች የተስማሙት በኢትዮጵያ መንግሥትና ሠራዊት ላይ ነው። ይህ ከተ.መ.ድ. ጉረቤቶች በኩታ ገጠም ጉረቤቶቻው ሠራዊት እንዳያሰማሩ የሚከተለውን መርህ (Principle of neutrality) ዓለም ሁሉ ተቀብሎት የፀጥታው ምክር ቤት የኢትዮጵያን ሠራዊት አቢዬ መዝመት ፕሮፌሰሩ ምን ይሉታል? አንድ ሀቅ አለ። ኢትዮጵያ በዲፕሎማሲው መስክ በአፍሪካ ተደማጭ ሆናለች። በተለያዩ የዓለምዓቀፉ መድረኮች የኢትዮጵያ አቋም የአፍሪካ ድምጽ መሆኑ በተደጋጋሚ ታይቷል። ለሱዳን ሰላም የተፈረመውን የሰላም ስምምነት (Comprehensive Peace

Agreement) ከረቂቁ ጀምሮ በማዘጋጀት ረገድ ኢትዮጵያ የመሪነት ሚና መጫወቷ ይታወቃል።

<u>ስድስተኛ</u>

ፕሮፌሰር መስፍን በመፅሐፋቸው ኤርትራ የሶማሊያን አሸባሪዎች የመርዳት አቅሙም ብቃቱም እንደሌላት ያስረዳሉ (ገጽ 134)። "ኤርትራ እንዴት ነው የሶማሊያን ሽብርተኞች ለመርዳት የሚችለው ያውም ባህር አቋርጦ ሄዶ?... ኤርትራ የሶማሊያን ሽብርተኞች የሚረዳ ሳይሆን እርዳታ የሚያስተላለፍ ነው ማለቱ የሚያስማማ ይሆናል።" ኤርትራ ለአሸባሪዎች ከሊብያ፣ ግብጽ፣ ኳታር እና የመሳሰሉት ሀገሮች ለሚደረግ እርዳታ መሸጋጋሪያ ብቻ ሳትሆን የሥልጠና፣ የመሳሪያ፣ የቀጥታ የሰው ኃይል ድጋፍ እንደምታደርግ የተባበሩት መንግሥታት የሞኒተሪንግ ሪፖርት ምስክር ነው። ዩ.አይ.ሲ በኢትዮጵያ ከተመታ በኋላ ማዘዣውን ከሞቃዲሾ ወደ አስመራ ማዞሩ ለማንም ሚስጥር አይደለም። በጦር መሣሪያ ደረጃም የኤርትራ መንግሥት ችግር የለበትም። ደርግ ኤርትራን ጥሎ ሲወጣ የተረከበው የነብስ ወከፍ መሣሪያ ብቻ ይበቃዋል። ኢትዮጵያን እስከወጋ ድረስ ደግሞ የማያስታጥቀው ኃይል የለም። የኤርትራ መንግሥት እብሪት ቆሞ የቀጥታ ወረራ ማድረግ እንደማይችል ከተረዳ በኋላ ሶማሊያን እንደሌላ ግንባር

ተጠቀማት፣ የቀጥታ ተዋናይ ሆነ እንጂ በማስፈፀም ተግባር ላይ ብቻ አልተሰማራም። ዞሮ ዞሮ ግን ፕሮፌሰሩ የሻዕቢያን ወንጀል ለማሳነስ አቀባባይ ነው ያሉለት የኤርትራ መንግሥት አቀባበለም፣ አሰለጠነም፣ በቀጥታ ጣልቃ ገባም፣ አተረማመሰም ሚናው ቁልጭ ያለች አፍራሽ ጣልቃ ገብነት ሲሆን ዓላማውም ኢትዮጵያ ናት። ኤርትራ አልሸባብን በመርዳት ለኢትዮጵያ የጐን ውጋት ከመሆን በዘለለ ለሶማሌዎች አስቦ አይደለም።

<u>ሰባተኛ</u>

ኢትዮጵያ በአፍሪካ ቀንድ የምዕራባዊያን ጥቅም አስካባሪ እየሆነች ነው፤ ወደ ሶማሊያም የገባችው ተከፍሏት ነው ይላሉ (ገጽ 138)። እስላማዊ ኅብረት ኢትዮጵያን ቢያስፈራም ትንኮሳ የሚባል አይመስለኝም፣ የሶማሊያ ጦር ከድንበሩ ሳያልፍ ኢትዮጵያ ወደ ሶማሊያ መግባቷ የጉዳዩ ባለቤት ማን እንደሆነ በገሀድ ያሳያል ይላሉ። በፀሐፊው እምነት ኢ.ህ.አ.ዴ.ግና የሚመራው መንግሥት በአፍቃሪ ምዕራባዊነት የሚታማ አይደለም። አብዩታዊ ዲሞክራሲና የኒዩሊብራል ለዚህ መጽሐፍ ፍጆታ ሲባል አንድ ተደርጓል። ምዕራባዊያን ዲፕሎማቶች የሚከሱት መንግሥት ወደ ምዕራብ ሳይሆን ወደ ኤሽያ በተለይም ቻይናና ሕንድ ሩጫ አበዛ በሚል ነው። እንዴት ሆኖ ነው መንግሥት የአሜሪካም፣ የሂይማን ዎች፣

የአሜንስቲ ኢንተርናሽናል ወዳጅ ተደርጎ የሚቀርበው? ፕሮፌሰሩ የያዙት በተለያየ ምዕራባዊያን እና እነሱ የሚያሽከረክሯቸው የብሪተንውድስ ተቋማት (የዓለም ባንክ፣ የዓለምዓቀፉ የገንዘብ ድርጅት) ላለፉት ሃያ ዓመታት ከኢትዮጵያ ጋር ያላቸው ውጣ ውረድ የበዛበት ግንኙነት ይህን አያሳይም:: መንግሥት እንደዛ ቢሆን ባንኩንም ቴሌውንም ሽጦ እንዳሉት በሆነና ከሚዘንብበት የዲፕሎማሲና የሚድያ ዘመቻ በዳነ ነበር:: ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ ሂስ የሚቀርብበት እንደ አርዩስ የሚወገዘው መሬት የሚሸጠውና የሚለውጠው በከርሰ መቃብሬ ላይ በማለቱ ነው::

የኢትዮጵያ የመከላከያ ኃይል ወደ ሶማሊያ የገባው ተከፍሎት ነው የሚለው የፕሮፌሰር ክርክር ውሃ አይቋጥርም:: መግባት ነበረበት/አልነበረበትም በሚለው ላይ እንደ ዜጋ ከመጽሐፉ ደራሲ የተለየ አቋም አለኝ:: በመጀመሪያ ኢትዮጵያ የአልቃይዳ ተከታዬች ጥቃት ዒላማ የሆነችው ከእንግሊዝም፣ ከስፔንም ከፈረንሳይም ቀድማ መሆኑ እንዴት ይዘነጋል? አሜሪካም ሆነ እነዚህ ሀገሮች አልቃይዳን "ፋሽን" ያህል ደጋግመው ያነሱት ከኒውዬርክ የመንትያ ሕንጻዎች ጥቃት በኋላ ነው:: ኢትዮጵያ የአሸባሪዎች የጥቃት ዒላማ የሆነችው ግን ከየትኛውም ሀገር በፊት ነው:: ይህን አስተያየት

የመንግሥት አቋም አድርጌ በመውሰድ መጥቀስ ካልተፈለገ አንድ ነገር ነው፡፡ ሀቁ ይኸው ይመስለኛል፡፡ አል ኢትሃድ አል እስላሚያ አዲስ አበባና ድሬዳዋን ያጋዩት ከዚያ በፊት ነው፡፡ ፕሮፌሰር ካልዘነጉት በስተቀር እ.ኤ.አ. 1996 የኢትዮጵያ የመከላከያ ሠራዊት ሶማሊያ ሉቅ ግዛት ድረስ ዘልቆ አል ኢትሃድን መደምሰሱ የቅርብ ጊዜ ትዝታ እኮ ነው፡፡ ሌላው የሶማሊያ እስላማዊ ኅብረት ምሳውን አዋሽ ራቱን ደግሞ አዲስ አበባ እንደሚያደርግ እየተናገረ ርዕሰ መዲናችንን እንደ ዩጋንዳ ዋና ከተማ ካምጠላ አጥቅቶ ንፁሐንን እስኪፈጅ መጠበቅ ነበረበት ዓይነት ክርክር ምን የሚሉት ነው፡፡ መንግሥት ትናንትም ዛሬም የዜጎቹን ደህንነት የመጠበቅ ግዴታ አለበት፡፡ መንግሥት የሚያደርገውን ሁሉ ስህተት አድርጌ መኮነን ምንም አስተማሪ አይደለም፡፡ ኢትዮጵያ በአሸባሪው ኃይል ላይ ጥቃት (preemptive attack) ፈጽማ አከርካሪውን በመስበሯ በሀገሪቱ ላይ የተጋረጠውን የፀጥታ ስጋት ቀርፋለች፣ ሶማሊያ ሌላዋ አፍጋኒስታን እንዳትሆን አድርጋለች፡፡ ዓለምዓቀፉ ማኅበረሰብ ለሶማሊያ ሰላም ትኩረት እንዲሰጥና የአፍሪካ የሰላም አስከባሪ ኃይል (አንሚ) በሀገሪቱ እንዲሰማራ ዕድል ፈጥሯል፡፡ ዩጋንዳ፣ ቡሩንዲ፣ ጅቡቲ ወታደሮቻቸውን ለማሰማራት ችለዋል፡፡ ይህ ከጣልቃ ገብነት ምን ፋይዳ ተገኘ

የሚለው የፕሮፌሰር ጥያቄ አይመልስ ይሆን? የኢትዮጵያ መንግሥት ገንዘብ ከተቀበለ ምን ያህል? መቼ? የት? ፕሮፌሰር የሚያውቁትን ቢነግሩን፡፡ ካልሆነም በሰማ በለው በእሳቸው ደረጃ አይጻፍም፡፡ አስተያየቱ ሂትለር እንድትታመን ከፈለክ ትልቅ ውሸት ዋሽ ያለውን ያስታውሰኛል፡፡ በዚህ የኢትዮጵያ ዘመቻ አልቃይዳ በመዳከሙ የሚጐዱ እንዳሉ ሁሉ የሚጠቀሙ አሉ፡፡ ኬንያ የጠላቴ ጠላት ወዳጄ በሚባለው ሂሳብ ተጠቃሚ በመሆኗ መንግሥት የኬንያ ተላላኪ ሆኗል፣ ገንዘብም ተቀብሏል ሊባል አይገባውም፡፡ የኢትዮጵያ ጦር ወደ ሶማሊያ በሚገባበት ዋዜማ አሜሪካ አስራ አንድ የጦር አበጋዞችን በማሰባሰብ የሰላም እና የፀረ- ሽብር ቅንጅት (Alliance for the Restoration of Peace and Counter-terrorism) የሚል ጥምረት በማቋቋም ተጠምዳ ነበር፡፡ የዚህ ቅንጅት ዓላማ ሶስት የአልቃይዳ መሪዎችን ማደን ነበር፡፡ እንኳን ገንዘብ ልትቀበል ኢትዮጵያና አሜሪካ ሼክ ሸሪፍ የሚመሩት መንግሥት ሞቃዲሾ እስኪገባ ድረስ ሰፊ ልዩነት ነበራቸው፡፡ ኢትዮጵያ የፀረ ሽብር ቅንጅትን መደገፍ እንደማያዋጣ የፀና እምነት ነበራት፡፡ አሜሪካ በተቃራኒው፡፡ የኢትዮጵያ መንግሥት በተባበሩት መንግሥታት እየተከፈለው በአሚሶም ጥላ ሥር እንዲሆን በቅርቡ የቀረበለትን ጥያቄ አለመቀበሉ በዚህ በመርህ

ላይ የተመሠረተ አቋሙ ማሳያ ነው:: የኢትዮጵያ መንግሥትም ወደ ሶማሊያ እንዳይገባ ተጽእኖ ታደርግ እንደነበር ይታወቃል:: ይህ ሌላኛው ግድፈት ነው::

<u>ስምንተኛ</u>

ሽብርና ሽብርተኛ በሚል ርዕስ ባሰፈሩት ጽሁፍ (ገጽ 77) ከፈረንሳይ ጋር ሲዋጉ የነበሩት አልጄሪያውያን ለፈረንሳይ ሽብርተኞች ለአልጄሪያውያን ደግሞ አርበኞች ነበሩ ይላሉ:: የአንዱ አሸባሪ ለሌላው አርበኛ የሚለውን ብሂል ያስታውሷል:: ተመራማሪው ወደ አፍሪካ ቀንድ ይመለሱና ወያኔ እና ሻዕቢያ ግን ከአርበኝነት ይልቅ ወደ ሽብርተኝነት የሚያደሉ ይመስላሉ ይላሉ:: ናቸው አይደሉም የሚለውን መነጋገር ለጊዜው እንተው:: በየትኛው ሚዛን እና በማን አይን ነው አሸባሪነታቸው:: ፕሮፌሰሩ አርበኛ ብለው እንዲገልጿቸው አይጠበቁም:: እርግጥ ነው ፈረንሳዬች አልጀሪያውያንን በአሸባሪነት እንደፈረጁ ሁሉ ሁለቱንም የቀድሞ ሽምቅ ተዋጊዎቹን በሽብር የሚከስ ቢኖር አይገርምም:: አለበለዚያ ፕሮፌሰር ቀመር የተሳሳተ ነው:: ፕሮፌሰሩ አሸባሪ የሚሏቸውን ቡድኖች ተወደደም ተጠላም በአርበኝነት የሚቀኙላቸው፣ የሚዘፍንላቸው ሕዝብ እንዳለ ቢገለጽ ስህተት አይሆንም::

በአጠቃላይ መጽሐፉ ውስጥ ተጠይቀው የማይመለሱ፣ ተጀምረው የማይጨረሱ በመሰለኝ እና ደሳለኝ የቀረቡ ነገሮች ቢኖሩም በጐም መጥፎም ታሪካችን መጻፍ ይገባዋል፡፡ ፕሮፌሰሩ ይህን በማድረጋቸው ሊመሰገኑ ይገባል፡፡ የተጻፈውን አንብቦ በሰለጠነ መንገድም ለሃጥያን የሚገባውን እየሰጡ መከራከርም ተገቢ ነው፡፡ እጣ ፈንታችን ይችው ሀገራችን ናትና፡፡ ማኅበረሰባችን ጽንፍ (polarized) አቋም ነው ያለው፡፡ ይወዳል ወይ ይጠላል፡፡ ያርቃል አልያም ይርቃል፡፡ በሚጠላው አካል ውስጥ ያለን ጠንካራ ጐን አያይም፡፡ የፕሮፌሰር መፀሐፍ አንድ ማሳያ ነው፡፡ ቢሆንም ጥላቻን መስበክ ቁም ነገር አይደለም፡፡ ስም እያነሱ ጭቃ መለጠፍ ለማን ይጠቅማል? መታበይ የአእምሮ ዳፍንትን ያስከትላል ይላሉ ፕሮፌሰር መስፍን፡፡ ትክክል፡፡ ስለኢትዮጵያዊ ጨዋነት አበክረው በሚሰብኩበት መጽሐፍ ጨዋነት የጐደለው ንግግር መጠ ቀማቸው አስፈላጊ አይደለም፡፡ ከእሳቸው አይጠበቅም፡፡ የወረዱ ቃላት ሳይጠቀሙ መጻፍ ይቻላል፡፡ ሰው ሃሳብ ካለው ለዘለፋ ጊዜ እና ቦታ የለውም፡፡ በመጨረሻም ለፕሮፌሰሩ መልካም ጤንነትና ረጅም ዕድሜ ሰጥቶ ወደፊትም የብዕራቸውን በረከት ለመቋደስ ያብቃን፡፡ ሰላም፡፡

meles.a2000@yahoo.com